# ሿ ሿ! ዳግም ምርጫ!

## (የምርጫ ጭውውት ክፍል ሁለት)

ደሞ ምርጫ! ሿ ሿ ዳግም ምርጫ!
እንዋጋም ብለን... ካልን ሰላም ብቻ
እርስ በእርስ መናቆር...ሳናቆም ጥላቻ
ውስጣችን ሳይጠራ...እንቅረብ ለምርጫ!
እስኪ ሰላም ይውረድ!...
እስኪ ውስኪ እንራጭ!...
ካልቻልን አሪንቻታ
ውስኪው ሰላም ይሁን- ፍቅር አሪንቻታ!

ምርጫ ቦርዱ ቢለኝ...አልኩት አላውቀውም
ፍርድ ቤቱስ ሲለኝ...አልኩት አላምነውም
ሰብዓዊ-መብት ሲል...አልኩት አልታደልንም
መከላከያ ሲል...ነገርኩት እንዲል ዝም
ተቃዋሚወችስ ሲል...አልኩት አሳመሙኝ
እየተጣሉ አልኩት...ለምን ብሎ ቢለኝ
ፌደራል ሲጠይቅ...ለሞቴ ፈራሁኝ
ታድያ ዝግጅቱስ?...አልኩት ምንም የለም
ማሸንፉስ ሲለኝ- እሱ አይታሰብም
ታድያ ትርፉስ ሲለኝ- አልኩት አላውቀውም።

ፏ! ፏ! ብሷል መለስ- ፏ! አለ እንጅ በሸገር
መተባበር ጠፍቶ...
መቻቻሉ ጠፍቶ
አገር ትቅደምቀርቶ
ቀና ማሰብ ቀርቶ.... ደግ መስራት ለአገር
ህዝብ ማዳን ቀርቶ...ዘራፍ ማለት ለአገር!

ጠላት ቢደነፋም- ቢበዛ እንቅፋቱ
አይከፋንም ነበር- ለህዝብ መሞቱ
እናንት ሳትስማሙ- ገብታችሁ ለምርጫ
አይፈስም አልልም- የደም አሪንቻታ።

ደሞ ምርጫ! ሿ ሿ ዳግም ምርጫ!
እንዋጋም ብለን... ካልን ሰላም ብቻ
እርስ በእርስ መናቆር...ሳናቆም ጥላቻ
ውስጣችን ሳይጠራ...እንቅረብ ለምርጫ!
እስኪ ሰላም ይውረድ!...
እስኪ ውስኪ እንራጭ!...
ካልቻልን አሪንቻታ
ውስኪው ሰላም ይሁን- ፍቅር አሪንቻታ!

እናንት ልብ ብትሉ- ግለኝነት ቀርቶ
አገር ማዳን ቢሆን- የዘንድሮው “ሞቶ”
ሕዝብ ማዳን ቢሆን- የዘንድሮው ጥሪት
ለፍትህ ተታግልን- ለፍትህ ብንሞት
እንኳን አንድ መለስ- በሕዝብ የተተፋ- የጋጠ-ወጥ አውራ
ገፍተን ባስወገድን- ግዙፉን ተራራ
ጣጥሰነው ገብተን....
ድሉን ተቀናጅተን...
በሕዝብ ለሕዝብ የቆመ- መሪያችንን መርጠን
ሰላም ብልፅግናን- ገንዝብ ባደረግን።

ደሞ ምርጫ! ሿ ሿ ዳግም ምርጫ!
አንዋጋም ብለን... ካልን ሰላም ብቻ
እርስ በእርስ መናቆር...ሳናቆም ጥላቻ
ውስጣችን ሳይጠራ...አንቅረብ ለምርጫ!
እስኪ ሰላም ይውረድ!...
እስኪ ውስኪ እንራጭ!...
ካልቻልን አሪንቻታ
ውስኪው ሰላም ይሁን- ፍቅር አሪንቻታ!

ዳግማዊ ዳዊት
የካቲት 2002 ዓ.ም.
Ethio_dagmawi@yahoo.com